# PRESS RELEASE

## የወጣቶች አግሮኢኮሎጂ ስታርትአፕ ውድድር-2026 ምዝገባ ተጀመረ!

የወጣቶች አግሮኢኮሎጂ ስታርትአፕ ውድድር-2026 የኢትዮጵያ ዘላቂ የምግብ ሥርዓትና ሥነ-ምሕዳራዊ ግብርና ሕብረት (Ethiopian Sustainable Food Systems and Agroecology Consortium - ESFSAC) ከDKA Austria እና Alliance for Food Sovereignty in Africa (AFSA) ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ እና በሸገር ሲቲ ለሚገኙ ወጣቶች ያዘጋጀው **የወጣቶች አግሮኢኮሎጂ ስታርትአፕ ውድድር 2026** ምዝገባ ዛሬ ሐምሌ 13/2018 በይፋ ተጀምሯል።

የ2025ቱን የወጣቶች አግሮኢኮሎጂ ስታርትአፕ ውድድር ስኬት መሠረት በማድረግ፣ የዘንድሮው ውድድር ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎቻቸውን የሚያቀርቡበት፣ ከባለሙያዎች እና ከአማካሪዎች ጋር የሚገናኙበት፣ ሙያዊ ትስስራቸውን የሚያስፋፉበት እና ለሥራዎቻቸው የላቀ እውቅና የሚያገኙበት መድረክ ለመፍጠር ያለመ ነው። ይህ ተነሳሽነት ዘላቂ እና አገር በቀል በሆኑ መፍትሄዎች አማካኝነት የኢትዮጵያን የምግብ ሥርዓት ለመለወጥ የወጣቶችን አመራር እና ተሳትፎ ለማጠናከር ይተጋል።

## የውድድሩ ዓላማዎች እና ይዘት

የወጣቶች አግሮኢኮሎጂ ስታርትአፕ ውድድር ዓላማ ለምግብ ሉዓላዊነት፣ ለዘላቂያዊነት (sustainability) እና ለማኅበረሰብ ደህንነት ሀገር-በቀል መፍትሔዎችን ማበርከትና ወጣቶች አግሮኢኮሎጂን እና ሀገር-በቀል ምግቦችን በማስተዋወቅ ረገድ የመሪነትን ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል ነው።

አመልካቾች ከሚከተሉት ሁለት የመወዳደሪያ ጭብጦች በአንዱ ወይም በሁለቱም መወዳደር ይችላሉ፦

- **የአግሮኢኮሎጂ ግብርና እና ፈጠራ (Agroecological Farming and Innovation)**፦ ይህ ምድብ ለአካባቢ ተስማሚ የሆኑ ዘላቂ የግብርና አሰራሮችን የሚያስተዋውቁ አዳዲስ ተነሳሽነቶችን እውቅና ይሰጣል። ይህም ኮምፖስት ማዘጋጀት፣ ኦርጋኒክ የአትክልት ምርት፣ የዘር ጥበቃ፣ የአገር ውስጥ ዘር ማምረት፣ ቨርሚኮምፖስቲንግ (የምድር ትል ማዳበሪያ አዘገጃጀት)፣ የግብርና ተረፈ ምርቶችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እና ዘላቂ ግብርናን፣ የአየር ንብረት መቋቋምን፣ የብዝሃ ሕይወት ጥበቃን እና ጤናማ ስነ-ምህዳርን የሚያጠናክሩ ሌሎች ፈጠራ-አከል ሥራዎችን ያጠቃልላል።
- **ጤናማ እና የሀገር-በቀል ምግቦች (Healthy and Indigenous Foods)**፦ ይህ ምድብ በባህላዊ የኢትዮጵያ የምግብ አዘገጃጀት መመሪያዎች፣ በዕፅዋትና በጤና ላይ ያተኮሩ የምግብ ምርቶች፣ ጤናማ የምግብ አቅርቦት አገልግሎቶች (catering) እና ስለ አገር በቀል የምግብ ባህልና ጤናማ አመጋገብ ግንዛቤን በሚፈጥሩ ዲጂታል መድረኮች አማካኝነት የተመጣጠነ እና ሀገር-በቀል ምግቦችን የሚያስተዋውቁ በወጣቶች የሚመሩ ጅምር የንግድ ሥራዎችን እና ተነሳሽነቶችን ይመለከታል።

## ማመልከት የሚችሉት እነማን ናቸው?

በአዲስ አበባ እና በሸገር ሲቲ የሚገኙ እድሜያቸው ከ18-35 ዓመት የሆኑ፣ አግሮኢኮሎጂን ወይም ጤናማ እና የሀገር-በቀል ምግብ ሥርዓቶችን የሚያጎለብት ጅምር የንግድ ሥራ (Startup) ላይ የተሰማሩ ወጣቶች ማመልከት ይችላሉ። ከወጣት ሴቶች እና በቂ ውክልና ከሌላቸው ማኅበረሰብ አባላት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን አጥብቀን እናበረታታለን።

## ሽልማቶች

በዳኞች ለተመረጡት አስር ተወዳዳሪዎች ለውድድሩ ጠቃሚ የሆኑ የዝግጅት ሥልጠናዎችን፣ ለሥራቸው እና ለአበርክቷቸው እውቅና፣ እንዲሁም ሥራቸውን የማስተዋወቅ እድል ያገኛሉ። በተጨማሪም፣ በውድድሩ ከ1 እስከ 3ኛ ለሚወጡ አሸናፊዎች የገንዘብ ሽልማት ይበረከትላቸዋል።

**1ኛ ደረጃ፡** 300,000 ብር
**2ኛ ደረጃ፡** 200,000 ብር
**3ኛ ደረጃ፡** 100,000 ብር

*ሁሉም ሽልማቶች የሚመለከተውን የመንግስት የታክስ ህግጋትና ደንቦችን መሰረት ያደረጉ ናቸው።*

## የማመልከቻ ጊዜ እና ዘዴ

የማመልከቻ ጊዜው ሐምሌ 13 እስከ 24 ቀን 2018 ነው። ለማመልከት፣ አመልካቾች ስለጅምር የንግድ ሥራቸው (Startup) የሚገልጽ የአንድ ደቂቃ ቪዲዮ መላክና በውድድሩ ገጽ ላይ የተዘጋጀውን የኦንላይን የማመልከቻ ቅጽ (ፎርም) መሙላት ይጠበቅባቸዋል።

የውድድሩ አጠቃላይ መረጃ፣ የመወዳደሪያ መስፈርቶች እና መመዘኛዎች በውድድሩ ገጽ ላይ ይገኛል፡- **https://esfsac-ethiopia.org/competition/**

የውድድሩ አዘጋጅ፣ የኢትዮጵያ ዘላቂ የምግብ ሥርዓትና ሥነ-ምሕዳራዊ ግብርና ሕብረት (Ethiopian Sustainable Food Systems and Agroecology Consortium - **ESFSAC**)፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ያላቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጥምረትና በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን በግንቦት 1 ቀን 2015 ዓ/ም እራሱን ችሎ የተመሠረተ ተቋም ነው። የተቋሙ አጠቃላይ ግብ የመንግሥት ባለድርሻ አካላትን እና ዜጎችን በማስተባበር አግሮኢኮሎጂን መሠረት ያደረጉ የምግብ ሥርዓቶችን ለማጎልበት ግንዛቤና እንቅስቃሴ በመፍጠር እንዲሁም መልካም ተሞክሮዎችን በማስተዋወቅ መርሆዎችን እና ልምዶችን በተጣጣመ መልኩ እንዲተገበሩ ማድረግ ነው። ለበለጣ መረጃ፡- www.esfsac-ethiopia.org

በዚህ የወጣቶች አግሮኢኮሎጂ ስታርትአፕ ውድድር እና በሌሎች ተግባራትም በኢትዮጵያ ዘላቂ የምግብ ሥርዓትን ለማጎልበት እና ሀገር-በቀል መፍትሔዎች ለማፍለቅ የምናደርገውን ጥረት ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ወደፊትም እንቀጥላለን። የሚዲያ አባላት፣ አጋር የልማት ድርጅቶች፣ የወጣት ማኅበራት እና የትምህርት ተቋማት የወጣቶች አግሮኢኮሎጂ ስታርትአፕ ውድድር ምዝገባ መጀመሩን በየአካባቢያችሁ ታደርሱልን ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን።

**ዶ/ር ባዩሽ ፀጋዬ**
ሥራ አስኪያጅ
የኢትዮጵያ ዘላቂ የምግብ ሥርዓትና ሥነ-ምሕዳራዊ ግብርና ሕብረት / Ethiopian Sustainable Food Systems and Agroecology Consortium (ESFSAC)

---

## የሚዲያ ተጠሪ

**Mahder Akalu**
Communication Expert
Email: mahder@esfsac-ethiopia.org | competition@esfsac-ethiopia.org
Telephone: +251 915 242 789
Website: https://esfsac-ethiopia.org/competition/